አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ መጋቢት ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፬

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th year No 47
Addis Ababa 26st of March, 2022

**ማውጫ**

**የመኖሪያ ቤት ኪራይ ጭማሪን ለ፺ ቀናት ለማገድ የወጣ የካቤኔ ደንብ ቁጥር ፻፳፪/፪ሺ፲፫ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣**

**ገጽ-------------------------------–፪ሺ፪፻፸፬**

**Regulation No. 122/2021 that was issued for the Suspension of Residential Housing Rental Increment for 90 days is hereby amended as follows.**

**Regulation Number 123/2022**

**Page----------------------------------------2274**

## ደንብ ቁጥር ፻፳፫/፪ሺ፲፬

## የመኖሪያ ቤት ኪራይ ጭማሪን ለ፺ ቀናት ለማገድ የወጣ ማሻሻያ ደንብ

በከተማው አስተዳደር ከግለሰብ የመኖሪያ ቤት ተከራይ የሆኑ ነዋሪዎች ላይ በአከራዮቻቸው ሚዛናዊ ከሆነው የቤት ኪራይ ዋጋ በላይ ጭማሪ እየተደረገ በመሆኑ አብዛኛው የከተማው ነዋሪ ተከራይ ለምሬት ከመዳረጉም ባሻገር የዋጋ ጭማሪው፣ ከአቅም በላይ የሆነ ኪራይ ማስከፈል፣ ተከራዮች ያለአግባብ በአከራዮቻቸው ፍላጎት ከተከራዩበት መኖሪያ ቤት እንዲወጡ ማድረግ፣ በአከራይ ተከራይ ግንኙነት አለመግባባት መፍጠሩ እና ለእንግልት መዳረጋቸው አሁንም የህዝብ እሮሮ እየቀረበበት በመሆኑ ችግሩ እስኪቃለል ድረስ በጊዜያዊነት የመኖሪያ ቤት ኪራይ ጭማሪን ማገድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## A Regulation to Provide for the Amendment for the Suspension of Residential Housing Rental Increment for 90 days

**WHEREAS,** the housing rental price has been increasing unfairly by landlords beyond the reasonable rental price on tenants, the request of unfair rental price, the inappropriate eviction of tenants based on the interest of the landlord, and the existence of conflict between tenants and landlords have created exasperation on the residents of the city and such has caused sufferings and intense dissatisfaction of the public; and therefore, it has been found necessary to temporarily suspend the residential housing rental increment until addressing the problem;



ያንዱ ዋጋ......... .
Unit price……….

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፸፬/፳፻፲፬ አንቀፅ ፺፪ መሰረት ይህን ማሻሻያ ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ " የመኖሪያ ቤት ኪራይ ጭማሪን ለ፺ ቀናት ለማገድ የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፳፪/፳፻፲፫ ን ለማሻሻል የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፳፫/ ፳፻፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ማሻሻያ**

የመኖሪያ ቤት ኪራይ ጭማሪን ለ፺ ቀናት ለማገድ የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፳፪/፳፻፲፫ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

የደንቡ አንቀጽ ፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ተተክቷል፡-

"**፬ ስለዕገዳ**

፩. በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ከየካቲት ፳ ቀን ፳፻፲፬ እስከ ነሃሴ ፲፱ ቀን ፳፻፲፬ በመኖሪያ ቤት ላይ የሚደረግ የኪራይ ዋጋ ጭማሪ የተከለከለ ነው፤

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም ዕገዳው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በከንቲባው ሊራዘም ይችላል፡፡"

**፫. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከ መጋቢት ፲፯ ቀን /፳፻፲፬ ዓ.ም. የጸና የሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፲፯ ቀን ፳፻፲፬ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 92 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 74/2021, the Cabinet of the Addis Ababa City government has issued this amendment Regulation.

1. **Short Title**

   This Regulation may be cited as: **"An Amendment for Regulation No. 122/2021 issued for the Suspension of Residential Housing Rental Increment for 90 days Regulation No. 123/2022."**

2. **Amendment**

   Regulation No. 122/2021 that was issued for the suspension of residential housing rental increment for 90 days is hereby amended as follows.

   Sub-Article (1) and (2) of Article 4 of the Regulation is cancelled and replaced by the following Sub-Article:

4. **About Suspension**

   "1. without prejudice to the provisions of other laws, a rental increment on residential houses from February 27th, 2022 to August 25th, 2022 is prohibited.

   2. notwithstanding to Sub-Article (1) of this Article, if the suspension is found necessary, it shall be extended by the Mayor."

5. **Effective Date**

   This Regulation shall enter into force as of this 26st day of March 2022.

**Done at Addis Ababa, this 26th day of March 2022**

**Adanech Abiebie**

**Mayor of Addis Ababa City**